## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰ/መ/ቁ 248615

ጥር 16 ቀን 2016ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካቾች፡-** 1. ኢንጅነር ጌታቸው እሸቱ

2. ወ/ሮ ሐረግነሽ መኮንን

**ተጠሪዎች፡-** 1. ዶ/ር በውቀቱ ታደሰ

2. ወ/ሮ መሰረት በረደድ

3. ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማሸጊያ ኃላ/የተ/የግል ማህበር

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ በሚል ሲሆን ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ክርክሩ የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይን የሚመለከት ሲሆን አመልካቾች የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለፍርድ አፈጻጸም የሰጠዉ ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል ለማሳረም ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡

የፍርድ አፈጻጸም ክርክር የጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኖቹ አመልካቾች ጥያቄ በተከፈተ መዝገብ ቁጥር 212760 ላይ ነው፡፡ ተጠሪዎች የፍርድ ባለዕዳ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ እንዲያስፈጽም የተጠየቀዉ ፍርድ የስር ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153204 ላይ በቀን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

27/6/2010ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማሻሻል በመዝገብ ቁጥር 155684 ላይ በቀን 24/01/2011ዓ.ም ወስኖ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 166294 ላይ በቀን 30/8/2011ዓ.ም የጸናዉ ዉሳኔ ነዉ፡፡

በአመልካቾች እንዲፈጸም የተጠየቀዉ የፍርድ ዉሳኔ ይዘትም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ መሰረት የካርታ ቁጥሩ 83/6 የቦታው ስፋት 3015 ካ.ሜ የሆነ በላዩ ላይ ከሰፈረው ከነሙሉ ንብረቱ የሽያጭ አካል ሳይሆን የ1ኛ አመልካች ነው በሚል የወሰነውን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የፀና በመሆኑ የካርታ ቁጥሩ 83/6 የቦታው ስፋት 3015ካ.ሜ የሆነ በላዩ ላይ ከሰፈረው ከነሙሉ ንብረቱ ተጠሪዎች ለቀዉ እንዲያስረክቧቸዉ እና ቀሪ የሽያጭ ገንዘብ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ እንዲታዘዝላቸዉ ነዉ፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈጻጸም ችሎቱም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያፀናው በመሆኑ ይህን ውሳኔ ለማስፈፀም የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ የሆነው ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማ ፋብሪካው በሚገኝበት ኦሮሚያ ክልል ቢሾፍቱ ከተማ የመሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ውሳኔው ለመፈጸም በሚያስችሉ ነጥቦች ላይ ይዞታ ልኬት በማድረግ ኣጣርቶ ምላሽ እንዲቀርብ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት፡- በአሁኑ 1ኛ አመልካች ስም ሁለት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታዎች የተሰጣቸው ሁለት ይዞታ ቦታዎች መኖራቸው፤ አንደኛው በ1983ዓ.ም የተሰጠ የካርታ ቁጥር 83/6 የሆነ የይዞታ ስፋቱ 3015ካ.ሜ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በ1996ዓ.ም የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 83/27 ይዞታ ስፋቱ 8290ካ.ሜ መሆኑን፤ 1ኛ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ፋብሪካ ይህንኑ ፋብሪካ ሲገነቡ ተለይቶ በተሰጣው ካርታ ቁጥሩ 82/27 በሆነው ስፋቱ 8290ካ.ሜ ላይ የይዞታውን ወሰን ጠብቀው መገንባት ሲገባቸው የይዞታዎቹ ወሰን ጠብቀው ባለመገንባታቸው የፋብሪካው 78 በመቶው ግንባታ በካርታ ቁጥር 83/6 በሆነው የይዞታ ስፋት 3015ካ.ሜ ላይ ቀሪው 22 በመቶ ደግሞ በካርታ ቁጥር 83/27 ይዞታ ስፋት 8290ካ.ሜ በሆነው መገንባቱን ለማረጋገጥ መቻሉን ገልጾ በውሳኔው መሰረት ለመፈፀም ሁለት አማራጮች በማስቀመጥ ማስፈጸም እንደሚቻል የቢሾፍቱ ከተማ የመሬት አስተዳደር ለአፈጻጸም ችሎቱ ምላሽ መስጠቱን እንዲሁም የባለሞያ ምስክርነት በመስማት የተለያዩ ትእዛዞት በመስጠት ማጣራት ካደረገ በኃላ የስር አፈጻጸም ችሎቱ የግራቀኙ ክርክር መነሻ ያደረገው የፋብሪካ ሽያጭ እንደሆነ እና የፋብሪካውን ሽያጭ መሰረት አድርጎ ይዞታው የአሁኑ አንደኛ አመልካች የሆነ ካርታ ቁጥር 83/6 ስፋቱ 3015ካ.ሜ የሆነ በሽያጭ እንዳልተላለፈ ነገር ግን የተሸጠው ጌት እሸት ዲተርጀንት ኃላ/የተ/የግ/ማ በካርታ ቁጥር 83/27 ስፋቱ 8290ካ.ሜ መሆኑን ተረጋግጦ ሲወሰን ፋብሪካው ስለመሸጡ እንጂ ፋብሪካው ያረፈበት ትክክለኛ ይዞታ የትኛው ይዞታ ላይ እንደሚገኝ ያልተለየ መሆኑን የፍርዱ መንፈስ ሲታይ የሽያጭ ውሉን እንዲፀና ተወስኖ ባለበት የሽያጭ ውሉን በሚቃረን መልኩ ፋብሪካው አካል ፈርሶ ለአሁኖቹ አመለካቾች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ይዞታ ይስተካከል የሚለው አንደኛው አማራጭ ባለመቀበል ሁለተኛው አማራጭ ወስዶ የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር መሬት አጠቃቀም ጽ/ቤት የካርታ ቁጥር 83/6 ስፋቱ 3015ካ.ሜ የሆነው ላይ የጌት እሸት ዲተርጀንት ፋብሪካ ያረፈበትን ለማካካስ ፋብሪካው ካረፈበት ይዞታ ውጭ ያሉ ከካርታ ቁጥር 83/6 እና 86/27 ውስጥ ያሉ ይዞታዎች ወደ አሁኑ አመልካቾች ይዞታ ተጠቃለው መጠኑ 3015ካ.ሜ እስኪሆን ድረስ በማሸጋሸግ ፍርድን እንዲያስፈጽም፡፡ በአፈጻጸም ሂደት ካርታ ማስተካከል የሚያስገድድ ከሆነ ካርታውን በማስተካከል ፍርዱን ያስፈጽም በሚል በአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 212760 በቀን 20/7/2015ዓ.ም ትእዛዝ በመስጠት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ አመልካቾች በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁኖቹን ተጠሪዎች መጥራት ሳያስፈልገው በፍሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት

የአመልካቾችን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ አድርጐታል፡፡

አመልካቾች ሀምሌ 12 ቀን 2015ዓ.ም አሻሽለው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህንኑ በመቃወም መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን ይዘቱም አጠር ባለ መልኩ ሲታይ፡- 1ኛ አመልካች በካርታ ቁጥሩ 83/6 የተመለከተው ስፋቱ 3015ካ.ሜ የሆነ ይዞታ በ1983ዓ.ም በመውሰድ የግል ፋብሪካ ፣መጋዘኖች፣የሽያጭ ሱቆች በመገንባት ወደ ስራ ከተገባ በኃላ ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማሸጊያ ኃላ/የተ/የግ/ማ ሰው ሆኖ የተመሰረተው በ1996ዓ.ም መሆኑን፤ የካርታ ቁጥር 83/27 ይዞታ ስፋት 8970ካ.ሜ የተወሰደውም በዚሁ ጊዜ በመሆኑ በእነዚሁ ሁለት ቦታዎች መካከል የ13 አመት ልዩነት ያለው በመሆኑ የካርታ ቁጥር 83/9 የተመለከተው ይዞታ ስፋት 3015ካ.ሜ ላይ የጌት እሸት ኬሚካል ማምረቻ ድርጅት አስቀድሞ የተገባና አሁንም ያለ መሆኑን ይህ ፋብሪካ የተሸጠው ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማ አካል ሳይሆን ራሱን የቻለ የ1ኛ አመልካች የግል ንብረት እንደሆነ፤ለአሁኖቹ ተጠሪዎች በሽያጭ የተላለፈው የካርታ ቁጥር 83/27 የይዞታ ስፋት 8290ካ.ሜ ላይ ያረፈው ይዞታ እንጂ በካርታ ቁጥር 83/6 በ3015ካ.ሜ ያረፈው ይዞታ እንዳልሆነ፤ የካርታ ቁጥር 83/6 የሆነው 3015ካ.ሜ የሆነው ይዞታና በዚሁ ይዞታ ላይ ያረፈው ሙሉ ንብረት የአሁኑ 1ኛ አመልካች የግል ሀብት መሆኑን ፍርድ አርፎበት እያለ የስር አፈጻጸም ችሎቱ በውሳኔው መሰረት ማስፈጸም ሲገባው ከውሳኔው ውጭ በሆነ መንገድ በካርታ ቁጥር 83/6 የተመለከተው 3015ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚገኘው ሙሉ ንብረት ተጠሪዎች እንዲረከቡ አመልካቾች ከዚህ ውጭ ያለው ባዶ ቦታ እንድንረከብ የሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ ለአፈጻጸም መሰረት የሆነው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 155684 የሰጠው ፍርድ በመሆኑ አፈጻጸሙ ይህንኑ ፍርድ ያገናዘበ

መሆን አለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ በታዘዘው መሠረት ተጠሪዎች መልስ ሰጥተዋል።

ተጠሪዎች ነሀሴ 09 ቀን 2015ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘቱ አጠር ባለ መልኩ ሲታይ፤- የቢሾፍቱ ከተማ መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት በፍ/ቤት ትዕዛዝ ባቀረበው ሪፖርት የጌት እሸት የዲትረጀንት ማምረቻና ማሸጊያ ፋብሪካ ግዙፍ ሕንፃ የተገነባው በካርታ ቁ.83/27 የቦታ ስፋት 8290 ካ.ሜ እና በካርታ ቁ.83/6 የቦታ ስፋት 3015 ካ.ሜ ላይ መሆኑን እና የፋብሪካው 78% 2590 ካ/ሜ የሆነው አካል በካርታ ቁ.83/6 የቦታ ስፋት 3015 ካ.ሜ ላይ ማረፉን፤ በካርታ ቁ.83/27 የቦታ ስፋት 8290 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሰፈረ ሌላ ፋብሪካ የሌለ መሆኑን መ/ቤቱ ከሪፖርቱ ጋር አያይዞ ያቀረበው እስኬች፤ የGIS እና የCIS ፕሪንት ሰነዶች በማያሻማ ሁኔታ በግልጽ የሚያሳዩ እና የሚያረጋግጡ ሲሆን በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ከዚሁ መ/ቤት እና ከሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ዳይሬክቶሬት የመጡ ሞያተኞችም በችሎት ቀርበው ይህንኑ እንዳረጋገጡ፤ አመልካቾች በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.153204 ላይ የፋብሪካው የሽያጭ ውል ይፍረስልን ብለው ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሆኖ የሽያጭ ውሉ አይፈርስም ተብሎ የተሰጠው ወሳኔ እና በተመሣሣይ የአክሲዮን ማስተላለፍ ቃለ ጉባኤም ህጋዊ ነው ተብሎ የተሠጠው ዉሣኔ እስከ ዛሬም ጸንተው ያሉ መሆናቸውን፤ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.166294 ላይ በ30/08/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሽያጭ ውል እና የአክሲዮን ማስተላለፊያ ቃለ ገባዔ ሕጋዊ መሆናቸውን አረጋግጦ የጌትእሸት ዲትረጀንት ማምረቻና ማሸጊያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ፋብሪካ አካል ያልሆነ በካርታ ቁ.83/6 የቦታ ስፋት 3015 ካ.ሜ የሰፈረ ቦታ የ1ኛ አመልካች ነው አለ እንጂ አመልካቾች እንደሚሉት በካርታ ቁ.83/6 የቦታ ስፋት 3015 ካ.ሜ በሆነው ይዞታ ላይ ያረፈው 78% 2590 ካ/ሜ የሆነው የፋብሪካው ግዙፍ አካል 1ኛ አመልካች ይረከቡ በሚል እንዳልወሰነ፤ አመልካቾች፤ የስር አፈጻጸም ችሎቱ ከካርታ ቁ.83/27 የቦታ ስፋት 8290 ካ.ሜ ላይ ፍርዱ ተቻችሎ እንዲፈጸም ለማድረግ ፋብሪካው የተገነባበትን ቦታ በባለሞያ እንዲታይ ከአደረገ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 378፤392 እና ሰ/ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 91622 ቅጽ 16 ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት የአፈጻጸሙን ምቹ ሁኔታዎች ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ ፍርዱ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ በመከተል የካርታ ቁጥር 83/6 ስፋቱ 3015 ካ/ሜትር ከሆነው ላይ የጌት እሸት ዲትረጀንት ማምረቻና ማሸጊያ ፋብሪካ ያረፈበትን ለማካካስ ከካርታ ቁ.83/27 ላይ ከሚካተት ክፍት ቦታ በማሸጋሸግ ፍርዱ እንዲፈጸም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ እና ይ/ሰሚው ፍ/ቤትም ይህን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመቀበል ማጽናቱ ይበልጡኑ የአመልካቾችን መብት የጠበቀ ፍትሀዊ የሆነ ውሳኔ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ባለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው አፈጻጸም ትእዛዝ ሊፀና ይገባል በሚል መልስ ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የፍርድ ዉሳኔዉን ለማስፈጸም በስር ፍርድ ቤት በተሰጠዉ ትእዛዝ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተፈጽሟል? ወይስ አልተፈጸመም? የሚል ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክር፣ እንዲፈጸም የተጠየቀዉን የፍርድ ዉሳኔ እና አግባብነት ያለዉን የሕግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ጉዳዩን እንደሚከተለዉ መርምረናል።

በመሰረቱ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን ስለ ፍርድ አፈጻጸም በሚደነግገዉ ሰባተኛ መጽሐፍ ስር ካሉ ድንጋጌዎች እንደምንረዳዉ የተፈረደለት ሰዉ ማመልከቻ በማቅረብ የፍርድ አፈጻጸም ሲጠይቅ ፍርዱን የሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት እንዲፈጸም የተጠየቀዉን ፍርድ መሰረት በማድረግ እና በዚህ መጽሐፍ ስር ባሉ ድንጋጌዎች የተዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ ማስፈጸም ይኖርበታል።በሌላ አገላለጽ ከድንጋጌዎች አቀራረጽ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የፍርድ አፈጻጸም ግብ ሥነ ሥርዓቱን በመከተል ፍርድ ተግባራዊ ማድረግ ወይም በተግባር መተርጎም ነዉ። በዚህ መሰረት ፍርዱን የሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈጸም በሚል የሚሰጠዉ ትእዛዝ ፍርዱን ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑንና የተወሰነላቸዉ ሰዎች የተወሰነላቸዉን ነገር እንዲያገኙ ለማድረግ የሚችል ተስማሚ ትእዛዝ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 378 እና 392/1 ስር የተደነገገዉ ያስገነዝባል። የፍርድ አፈጻጸሙ በእነዚህ ድንጋጌዎች በተዘረጋው ሥርዓት አግባብ በመመራት ካልሆነ በስተቀር በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ሕጋዊ ባልሆነ እና ውሳኔውን ውጤት አልባ ወይም ሌላኛውን ወገን(ባለዕዳዉን) ፍርዱ ያልጣለበትን ኃላፊነት እንዲሸከም በሚያድርግ መልኩ ሊመራ የሚችልበት አግባብ አይኖርም።በዚህ አግባብ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ ፍርዱን ተግባራዊ ማድረግ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ ማስፈጸም ስለመቻላቸዉ ዋነኛ ማረጋገጫ ከመሆኑም በተጨማሪ ነጻነቱ የተጠበቀ እና የሕዝብ አመኔታ ያለዉ ፍርድ ቤት ለመኖሩ ማሳያ ሆኖ የሚያገለግል የዳኝነት ሥራ ተግባር ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ነዉ። በተጨማሪም ሥነ ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ አንድን ፍርድ ማስፈጸም የሥነ ሥርዓት ሕጉ የቆመለት በምክንያታዊ ጊዜ፣በዉስን የሰዉ ሀብትና ወጪ ለክርክሮች እልባት የመስጠት ዓላማ እንዲሳካ ያደርጋል።

ማንኛዉም የፍርድ ዉሳኔ እንዲፈጸም ሲጠየቅ ፍርድ ቤቱ የፍርድ ባለዕዳዉን ጠርቶ በፍርዱ መሰረት የማይፈጽምበት ምክንያት መኖር አለመኖሩን ከመረመረ(ከጠየቀ) እና የፍርድ ባለዕዳዉ በመሀላ ቃል አስደግፎ የሚሰጠዉን መልስ ከሰማ በኂላ የፍርድ ባለዕዳዉ እንደፍርዱ የማይፈጽምበት ምክንያት ያለመኖሩን ሲያረጋግጥ ለአፈጻጸሚ ተስማሚ በሆነ መንገድ ትዕዛዝ በመስጠት የፍርዱን ይዘትና መንፈስ ተከትሎ ፍርዱን ማስፈጸም ይኖርበታል (የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 386 እና 392/1 ይመለከቷል) ። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ አንድን የፍርድ ዉሳኔ የሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት የፍርድ ዉሳኔዉን ይዘት አድማስ ባገናዘበ መልኩ ስለፍርዱ አፈጻጸም ተስማሚ የሆነ መንገድ በመለየት ፍርዱን የማስፈጸም ሥልጣን ያለዉ ስለመሆኑ ነዉ።በተጨማሪም ፍርዱን የሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 392/2 ስር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንደተደነገገዉ የፍርድ ባለዕዳዉ በማናቸዉም ምክንያት ቢሆን ፍርዱን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመፈጸም የማይችል መሆኑን ከተረዳ ፍርዱ ሳይፈጸም እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር ህዳር 18 ቀን 2015ዓ.ም 3ኛ ተጠሪ የሆነው እና በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ላይ ማሻሻያ የተደረገበት ቃለጉበኤ ለማስፈረስ ካልሆነም የሽያጩን ቀሪ ክፍያና የተቋረጠ ጥቅም ለማስከፈል እንዲሁም ከህግ አግባብ ውጪ ተጠሪዎች የያዙት 3015ካ.ሜ ይዞታ ላይ ተተክለው የሚገኙ ኬሚካል ኢንዱስትሪ ማሽኖች እና ሕንጻዎች የአመልካቾች ንብረት በመሆናቸው በነበሩበት ሁኔታ በመረከብ ያጡት ጥቅም ጭምር ለማስከፈል በተጠሪዎች ላይ የመሰረቱትን ክስና የተደረገዉን ክርክር እንዲሁም ማስረጃዎችን መርምሮ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153204 ላይ በቀን 27/06/2010ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ፡-

1. የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ የሆነው ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማ አስመልክቶ ህዳር 18 ቀን 2005ዓ.ም የተደረገው ሽያጭ ውልና ይህን ውል ተከትሎ ታህሳስ 16 ቀን 2005ዓ.ም የአክስዮን ድርሻ እና የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ ፋብሪካ ከአሁኖቹ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች(ሻጮች) ወደ አሁኖቹ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለማዞር/መመስረቻ ጽሁፍን ለማሻሻል/የተያዘው ቃለጉባኤ በህግ ፊት የጸና እና ፈራሽ ሊሆን ወይም ሊሰረዝ አይገባም፡፡

2. የአሁኖቹ ተጠሪዎች ከሽያጩ ውስጥ ያልከፈሉትን 17699952/አስራ ሰባት ሚልዮን ስድስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሀምሳ ሁለት ብር/ ውሉ ከተደረገበት ህዳር 18 ቀን 2005ዓ.ም ጀምሮ በዋና ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለአሁኖቹ አመልካቾች ሊከፍሉ ይገባል፡፡

3. የአሁኖቹ ተጠሪዎች ሁለት በኤሌክትሪክ የሚሰሩት ሮሊ ባሶችንና አንድ ኤኔትሪ መኪና ከነተሳቢው የአሁኖቹ አመልካቾች የባለቤትነት ሊብሬ ይዘው ሲቀርቡ ባሉበት ሁኔታ እንዲያስረክቡ ሆኖም የእርጅና ዋጋ እና የተቋረጠ ጥቅም የመክፈል ኃላፊነት የለባቸውም፡፡

4. በ1ኛ አመልካች ስም በቢሾፍቱ ከተማ ቀበሌ 01 በ3015ካ.ሜ ላይ የሰፈሩት ንብረቶች የተሸጠው የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ የሆነው ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማ አካል ነው በሚል ወስኗል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በማሻሻል በ1ኛ አመልካች ስም በቢሾፍቱ ከተማ ቀበሌ 01 በ3015ካ.ሜ ላይ የሰፈሩት ንብረቶች የተሸጠው የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ የሆነው ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማ አካል ነው የሚለውን የውሳኔ ክፍል ብቻ በመሻር ይህ ይዞታና ንብረት የአሁኑ 1ኛ አመልካች ነው በማለት ሲወስን ቀሪዎች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት በመዝገብ ቁጥር 155684 ላይ በቀን 24/01/2011ዓ.ም ውሳኔ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሰጥቷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ በሰ/መ/ቁ 166294 ላይ በቀን 30/8/2011ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ በመጽናት ወስኗል፡፡ ለፍርድ አፈጻጸሙ መሰረት የሆነውም ይሔው በካርታ ቁጥር 83/6 የሆነው 3015ካ.ሜ ይዞታና በላዩ ላይ የሰፈሩት ንብረቶች የሽያጭ አካል አይደሉም ተብሎ በተሰጠዉ ውሳኔ መሰረት አመልካቾች ይህንኑ ይዞታ በላዩ ላይ ከሰፈሩት ንብረቶች ጋር አስለቅቀዉ ለመረከብ ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡

አመልካቾች እንዲፈጸምላቸዉ የጠየቁትን ፍርድ ለማስፈጸም የፍርድ ዉሳኔዉን ሙሉ ይዘት ማየቱ ግድ ይላል፡፡ የግራ ቀኙ ግንኙነት 3ኛ ተጠሪ የሆነው ጌት እሸት ዲርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማ ሽያጭ ውል ስምምነት መሰረት ያደረገ መሆኑን ተረጋግጦ የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ የሆነው ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማ አስመልክቶ ህዳር 18 ቀን 2005ዓ.ም ከተጠሪዎች ጋር ያደረጉት ሽያጭ ውልና ይህን ውል ተከትሎ ታህሳስ 16 ቀን 2005ዓ.ም የአክስዮን ድርሻ እና የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ ፋብሪካ ከአሁኖቹ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች(ሻጮች) ወደ አሁኖቹ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለማዞር/መመስረቻ ጽሁፍን ለማሻሻል/የተያዘው ቃለጉባኤ በህግ ፊት የጸና ስለሆነ ሊፈርስ ወይም ሊሰረዝ አይገባም በሚል የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ክፍል በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ሆነ በሰበር ችሎቱ ያልተሻረና ፀንቶ የሚገኝ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል በካርታ ቁጥር 83/6 የሚታወቅ የመሬት ይዞታ ስፋቱ 3015 ካ.ሜ ሲሆን በዚህ ይዞታ ላይ በእላዩ ላይ ካለዉ ሙሉ ንብረት ጋር የሽያጭ አካል አለመሆኑና የ1ኛ አመልካች ንብረት እንደሆነ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተወሰነ እና በሰበር ችሎት በተሰጠ ዉሳኔም የፀና ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የሸጡት በካርታ ቁጥሩ 83/27 የሆነ 8290ካ.ሜ ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ጌት እሸት ዲርጀንት ማምረቻ እና ማከፈፊያ ፋብሪካ መሆኑ እና በካርታ ቁጥር 83/6 የሆነ 3015ካ.ሜ ይዞታ በይዞታው ላይ ከሰፈሩት ሙሉ ንብረቶች የሽያጩ አካል ሳይሆኑ የ1ኛ አመልካች የግል ንብረት ናቸው በሚል መወሰኑ አከራካሪ አይደለም፡፡

ከእነዚህ ውሳኔዎች መረዳት እንደሚቻለው በ3ኛ ተጠሪ ስም ማለትም ጌት እሸት ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማ በሚል የተቋቋመውን ፋብሪካ በሽያጭ ለማስተላለፍ በግራ ቀኝ መሀከል የተደረገዉ የሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም በሚል መወሰኑ የሽያጭ ዉሉ በፍርድም ጭምር ጥበቃ ተደርጎለታል፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ መነሻ ይህንን ዉል ዉጤት አልባ የሚያደረግ የፍርድ አፈጻጸም መንገድ መከተል ሕግ ጥበቃ ያደርግልናል፤ በፍርድ ቤትም እናስፈጽማለን በሚል እምነት የተደረገ ዉል ወይም ሕጋዊ ግብይት ዉጤት እንዳይኖረዉ ማድረግ ስለሚሆን ተቀባይነት ሊኖረዉ የሚገባ የፍርድ አፈጻጸም መንገድ አይሆንም፡፡ እንዲሁም አመልካቾች ስፋቱ 3015 ካ.ሜ የመሬት ይዞታ እና በዚህ ይዞታ ላይ ያሉትን ንብረቶች (በክሳቸዉ ዘርዝረዉ የጠቀሱትንና በኋላም በፍርድ ዉሳኔዉ ላይ የተመለከቱትን ሙሉ ንብረቶች) ለተጠሪዎች በሽያጭ አለማስተላለፋቸዉ ተረጋግጦ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንዲለቁ በተወሰነዉ መሰረት በማስፈጸም ለአመልካቾች የንብረት መብት የተደረገዉን ጥበቃ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስፈጸም ወይም ከግብ ማድረስ ይገባል፡፡ ስለሆነም የአፈጻጸም ክርክሩም መመራት ያለበት አንዱን የውሳኔ ክፍል ብቻ ለይቶ በማየት ሳይሆን እንደአጠቃላይ የፍርድ ዉሳኔዉን ሙሉ ይዘትና መንፈስ በተከተለ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡

ፍርዱን እያስፈጸመ ያለዉ የስር ፍርድ ቤትም ከአመልካቾች በሽያጭ ለተጠሪዎች የተላለፈው 3ኛ ተጠሪ የሆነው ፋብሪካ የሚገኘው በሽያጭ ውሉ በተጠቀሰው ካርታ ቁጥር 83/27 በሆነው 8290ካ/ሜ ላይ ብቻ ሳይሆን 78 በመቶው የፋብሪካ ግንባታ የሚገኘው በካርታ ቁጥር 83/6 በሆነው 3015ካ.ሜ ላይ እንደሆነ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ሊታይ የሚገባው ነጥብ በካርታ ቁጥሩ 83/6 የሆነው 3015ካ.ሜ በላዩ ላይ ከሰፈረው ሙሉ ንብረት ጋር የሽያጭ አካል ሳይሆን የ1ኛ አመልካች ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ አመልካቾች በሽያጭ ለተጠሪዎች ያስተላለፉት ፋብሪካ በ3015ካ.ሜ ላይ እንደሚገኝ በተረጋገጠ ጊዜ ለ1ኛ አመልካች ሊፈጸም የሚገባው በካርታ ቁጥር 83/6 የተጠቀሰው 3015.ሜ ይዞታ እና በዚሁ ይዞታ ላይ የሚገኘው 78 በመቶ የሆነው የፋብሪካ አካል ጭምር ነው ወይስ ከፋብሪካው ውጭ ያለው 3015ካ.ሜ ይዞታና የፋብሪካዉ አካል ያልሆነ ማንኛውም ንብረት ታክሎበት የሚለው ነው፡፡

አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት የካርታ ቁጥር 83/6 የተመለከተው ይዞታ ስፋት 3015ካ.ሜ ላይ የጌት እሸት ኬሚካል ማምረቻ ድርጅት አስቀድሞ የተገነባ ፋብሪካ አሁንም ያለ መሆኑን ይህ ፋብሪካ የተሸጠው 3ኛ ተጠሪ የሆነው ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማ አካል ሳይሆን ራሱን የቻለ የ1ኛ አመልካች የግል ንብረት እንደሆነ፤ የካርታ ቁጥር 83/6 የሆነው 3015ካ.ሜ የሆነው ይዞታና በዚሁ ይዞታ ላይ የሰፈረው ሙሉ ንብረት የአሁኑ 1ኛ አመልካች የግል ሀብት ነው ተብሎ ፍርድ አርፎበት እያለ የስር አፈጻጸም ችሎቱ ከውሳኔው ውጭ በሆነ መንገድ በካርታ ቁጥር 83/6 የተመለከተው 3015ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚገኘው ሙሉ ንብረት አመልካቾች ባዶ ቦታ እንድንረከብ ትእዛዝ መስጠቱ ተገቢነት የለውም በሚል ነዉ፡፡ ሆኖም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔውን ለማስፈፀም ባደረገዉ ማጣራት ከቢሾፍቱ መሬት አስተዳደር ወደ ቦታው ባለሞያ በመላክ ልኬት በማድረግ አጣርቶ በሰጠው ምላሽ የተረጋገጠው ፍሬነገር በካርታ ቁጥር 83/6 እና ካርታ ቁጥር 83/27 የሚታወቁ ሁለቱ ይዞታዎች እንዳሉ ነገር ግን በእነዚህ ይዞታዎች ላይ ራሳቸው የቻሉ ሁለት ፋብሪካዎች እንደሌሉ፤ በእነዚህ ይዞታዎች ላይ የተሸጠው ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ አንድ ፋብሪካ ብቻ እንደሚገኝ፤ 78 በመቶ የሆነው የፋብሪካው ግንባታ የሚገኘው በሽያጭ ውሉ በተገለጸው ካርታ ቁጥር 82/27 ይዞታ ስፋት 8290ካ.ሜ ላይ ሳይሆን የካርታ ቁጥር 83/6 በሆነው 3015ካ.ሜ ላይ መሆኑን፤ በሽያጭ ውሉ በተጠቀሰው ካርታ ቁጥር 86/27 ይዞታ ስፋት 8290ካ.ሜ በሆነዉ ይዞታ ላይ 22 በመቶ የሆነው የፋብሪካ ግንባታ ብቻ እንደሚገኝ መረጋገጡን፤ ይህም ሊሆን የቻለው 1ኛ አመልካች ሁለቱን ይዞታዎች ካገኙ በኃላ ፋብሪካው እንዲገነባ ተለይቶ በተሰጣቸው ይዞታ ላይ የካርታዎቹን ወሰን ጠብቀው ፋብሪካውን መገንባት ሲገባቸው ይዞታዎቹን በመቀላቀል የይዞታ ወሰን ሳይጠብቁ ፋብሪካውን በመገንባታቸው ምክንያት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በተጨማሪም ይህ ሰበር ችሎት በሁለቱም ይዞታዎች ላይ የተለያየ ፋብሪካ ያለ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ግራቀኙ በችሎት በመጠየቅ ባደረገው ማጣራት በአመልካቾች በኩል የ1ኛ አመልካች የግል ይዞታ ተብሎ በተወሰነው በካርታ ቁጥር 83/6 በሆነው 3015ካ.ሜ ይዞታ ላይ በአንድ በኩል ራሱን የቻለ ፋብሪካ አለ በሚል በሌላ በኩል ከተሸጠው ፋብሪካ ጋር ተመሳሳይ ምርት የሚያመርት ፋብሪካ እንደሆነ በመግለጽ ወጥነት በሌለው መልኩ የሚከራከሩ ቢሆንም በሁለቱም ይዞታዎች ላይ 3ኛ ተጠሪ የሆነው ፋብሪካ ብቻ መኖሩ ከዚህ ፋብሪካ ውጭ ሌላ ፋብሪካ አለመኖሩ በስር ፍርድ ቤቶች የተደረሰው ድምዳሜ ተገቢነት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል በካርታ ቁጥር 86/6 የይዞታ ስፋቱ 3015ካ.ሜ የሆነ በዚሁ ይዞታ ላይ ያለው ማንኛውም ንብረት ጋር የሽያጭ ኣካል ሳይሆን የ1ኛ አመልካች ነው በሚል በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተወስኖ በሰበር ችሎቱ የፀናው የውሳኔ ክፍልም ቢሆን በ3015 ካ.ሜ ላይ የሰፈረ ማንኛውም ንብረት በሚል መወሰኑ ውሳኔ ካረፈበት በሽያጭ ከተላለፈው ፋብሪካ ውጭ ያለ ማንኛውም ንብረት ለማለት እንጂ የፋብሪካ ሽያጭ ውሉ እንዲፀና በተወሰነበት ሁኔታ አመልካቾች ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በሽያጭ ያስተላለፉትን ፋብሪካ ጭምር የ1ኛ አመልካች የግል ንብረት ነው ማለት አለመሆኑን ከዋናው ፍርድ አጠቃለይ ይዘት በቀላሉ መረዳት የሚቻል ነው፡፡

በእነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንጻር አመልካቾች 3ኛ ተጠሪ የሆነው ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻ እና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማ ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በመሸጥ በግራቀኙ መሀከል ያደረጉት ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም በሚል ተወስኖ ውሳኔው ፀንቶ ባለበት፤ የፋብሪካው ግንባታ ያረፈበት አብዛኛው ይዞታ በካርታ ቁጥር 83/6 በሆነው 3015ካ.ሜ ላይ ስለመሆኑ በተረጋገጠበት ፤ እንዲሁም አመልካቾች እንደሚሉት በካርታ ቁጥር 83/6 በሚታወቅ ይዞታ ላይ ራሱን የቻለ ሌላ ፋብሪካ ሳይሆን ያለው በሽያጭ ያስተላለፉት 78 በመቶ የሆነው ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ፋብሪካ አካል የሆነ ግንባታ መሆኑና ከዚህ ውጭ ሌላ ፋብሪካ በቦታው ላይ አለመኖሩን የስር ፍርድ ቤቶች ባደረጉት ማጣራት በተረጋገጠበት ሁኔታ፤ በዚሁ የፍርድ ውሳኔ የጸናዉን የፋብሪካ ሽያጭ ውል አፈጻጸም ውጤት አልባ በሚያደርግ መልኩ በካርታ ቁጥር 83/6 በሚታወቀዉ 3015ካ.ሜ ላይ እንደሚገኝ የተረጋገጠው 78 በመቶ የሆነው የፋብሪካውን አካል ጭምር እንድንረከብ የአፈጻጸም ትእዛዝ ሊሰጥ ይገባ ነበር በሚል አመልካቾች የሚቀርቡት መከራከሪያ የዋናውን ውሳኔ ይዘትና መንፈስ ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ አመልካች ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በሽያጭ ያስተላፉትን 3ኛ ተጠሪ የሆነው ጌት እሸት ዲተርጀንት ኃ/የተ/የግ/ማህበር ምንም እንኳ በሽያጭ ውሉ ፋብሪካው ካርታ ቁጥር 83/27 ይዞታ ስፋት 8290ካ.ሜ እንደሚገኝ የተገለፀ ቢሆንም በተጨባጭ የፋብሪካው ሙሉ ግንባታ የተገነባው በሽያጭ ውሉ በተጠቀሰው ካርታ ቁጥር 83/27 ይዞታ ስፋት 8290ካ.ሜ ላይ ሳይሆን 78

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመቶው የካርታ ቁጥር 82/6 በሆነው 3015ካ.ሜ መሆኑን በማረጋገጥ ፣ የቢሾፍቱ መሬት አስተዳደር ሁለት ሙያዊ አማራጮች በማስቀመጥ የላከለትን ማብራሪያ መሰረት በማድረግ የፍርዱን መንፈስ በመከተል ከአንደኛው ይዞታ ወደ ሌላኛው ይዞታ ገብቶ የተገነባው የፋብሪካው አካል እንዲፈርስ በማድረግ ማስፈጸሙ ከዋናው ፍርድ መንፈስ መራቅ ነው በማለት ሁለተኛውን አማራጭ ወስዶ የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር መሬት አጠቃቀም ጽ/ቤት የካርታ ቁጥር 83/6 ስፋቱ 3015ካ.ሜ የሆነው ላይ የጌት እሸት ዲተርጀንት ፋብሪካ ያረፈበትን ለማካካስ ከካርታ ቁጥር 83/27 ላይ ከሚካተት ክፍት ቦታ በማሸጋሸግ ፍርድን እንዲያስፈጽም እና በአፈጻጸም ሂደት ካርታ ማስተካከል የሚያስገድድ ከሆነ ካርታውን እንዲያስተካክል የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ትእዛዝም ሆነ በዚህ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካቾች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመሰረዝ የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 392/1 ስር በተዘረጋዉ ሥነ ሥርዓት መሰረት በተቻለ መጠን የፍርድ ዉሳኔዉን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ተስማሚ መንገድ በመከተል ፍርዱን ማስፈጸማቸዉን የሚያሳይ እንጂ ከዋናው የፍርድ ውሳኔ ዉጭ የሆነ የፍርድ አፈጻጸም ትእዛዝ ሰጥተዋል የሚያሰኝ ባለመሆኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ዉሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 212760 ላይ መጋቢት 20 ቀን 2015ዓ.ም የሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 245822 ላይ በቀን 24/9/2015 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በሰበር ስነ- ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ሀ) መሰረት በአብላጫ ድምጽ ፀንተዋል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. በቀድሞ ካርታ ቁጥር 83/6 የሆነ 3015ካ.ሜ ይዞታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 414 መሰረት ጥቅምት 22 ቀን 2016ዓ.ም በዚህ መዝገብ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ክርክሩ እልባት ያገኘ በመሆኑ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይጻፍ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተራ ቁጥር 2 የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫዉ ድምጽ የስር ፍ/ቤቶችን የአፈጻጸም ዉሳኔ በማጽናት በሰጠዉ ዉሳኔ ባለመስማማት በሀሳብ ተለይቻለዉ፤ የልዩነት ሀሳቤን እንደሚከተለዉ አሰፍራለሁ፡፡

አብላጫዉ ድምጽ የፍርድ አፈጻጸም ሥርዓትን ወይም የፍርድ አስፈጻሚዉን ፍ/ቤት ስልጣን አስመልክቶ በፍርዱ የሕግ ትንታኔ ክፍል በአግባቡ እንደገለጸዉ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠ ፍርድ እንደ ፍርዱ መፈጸም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ሲሆን የፍርድ አፈጻጸም ስርዓት ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በእራሱ አማካኝነት ወደ ተግባር ወይም ውጤት የሚለውጥበት ስርአት መሆኑን፤ የተሰጠ ውሳኔ የማይፈፀምበት ሕጋዊ ምክንያት መኖር ያለመኖሩም በፍርድ ቤቱ ታይቶ ተገቢው እልባት የሚሰጥበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነዉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 91622 እና በሌሎች መዛግብት ገዥ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ ዉጪ ከተሰጠዉ ፍርድ በመዉጣት አዲስ መብት በሚፈጥር ወይም በፍርድ የተረጋገጠን መብት በሚያሳጣ መልኩ ያልተሰጠ ፍርድ ወይም ዉሳኔ የአፈጻጸም ዉሳኔ ተሰጥቶበት የሚፈጸምበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

በተለይ ፍርዱ ወይም ዉሳኔዉ የሚመለከተዉ የማይንቀሳቀስ ንብርት የማስረከብን ጉዳይ ሲሆን እንደፍርዱ የሚፈጸመዉ በዉሳኔዉ ላይ የተመለከተዉን ንብረት የፍርድ ባለገንዘቡ ራሱ ወይም የወከለዉ ሰዉ እንዲረከብ በማድረግ ነዉ በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 402(1) በግልጽ ደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለዉ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የተሰጠዉ ፍርድ እንደሌላዉ የሚንቀሳቀስ ንብረት እንደነገሩ አመቺነት ተብሎ ንብረቱ ካልተገኘ ንብረቱን በመተካት ወይም ወደ ገንዘብ እንዲቀየር ተደርጎ ተካክሶ እንዲፈጸም የሚደረግ ሳይሆን የማይንቀሳቀስዉን ንብረት ራሱን በማስረከብ ወይም በመረከብ ብቻ የሚፈጸም ነዉ፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የተሰጠዉ ፍርድ ላይፈጸም የሚችለዉ ወይም ከፍርዱ ወይም ከዉሳኔዉ በተለየ ሁኔታ ተሻሽሎ ሊፈጸም የሚችለዉ በተለይ ከፍርድ በኃላ ንብረቱ በመዉደሙ ፍርዱ ሊፈጸም የማይቻል ሲሆን ወይም ፍርዱን የሰጠዉ አካል የጸና ዉሳኔ ለመስጠት የማይችል በመሆኑ ዉሳኔዉ እንዳልተሰጠ የሚቆጠር ሆኖ ሲገኝ ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጪ በዋናዉ ፍርድ ተሰጥቶ በይግባኝ ወይም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በሌላ አግባብ ያልታረም ግልጽ የሆነ የፍርድ ባለዕዳዉን መብት የጣሰ ፍትህን ያዛባ ዉሳኔ እንኳ ቢኖር ፍርድ አስፈጻሚዉ ፍ/ቤት ዉሳኔዉ ግልጽ እስከሆነ ድረስ እንዳለ ከማስፈጸም በቀር የዋናዉን ፍርድ ስህተት ለማረም ጥረት ማድረግ የለበትም፡፡ እንዲሁም ፍርድ አስፈጻሚዉ ፍ/ቤት ፍርዱን ተርጉሞ በማስፈጸም ሰበብ በዋናዉ ፍርድ ተፈጽሟል ብሎ የሚያምነዉን ስህተት በአፈጻጸም ማረም የለበትም፡፡ ምክንያቱም አንድ ፍርድ አስፈጻሚ ፍ/ቤት በዋናዉ ፍርድ ተፈጽሟል ብሎ ሚያምነዉን የፍትሕ መዛባት በአፈጻጸም ወቅት ለማረም የሚጥር ከሆነ የዳበረ የፍርድ አፈጻጸም መርህ የሆነዉን ፍርድ አስፈጻመዉ ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ የተሰጠዉን ዉሳኔ ለማረም መጣር የለበትም ወይም ስልጣኑ የለዉም /"the Excuting Court cannot go or has no jurisdiction to go behind the Decree`/ የሚለዉን ሊጥስ ስለማይገባ ነዉ፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ በተጨማሪ አንድ ሰዉ በፍ/ቤት ተከራክሮ በአንድ ንብረት የባለቤትነት መብቱ ተረጋግጦለት እያለና ፍርዱም ሊፈጸም የሚችል ሆኖ ሳለ ፍርድን በማስፈጸም ሰበብ በተለይ ፍርድ ያረፈበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳጣት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ-መንግስት አንቀጽ 37(1) ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ዉሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለዉ የሚለዉን ፍትሕ የማግኘት መብት የተሟላ እንዳይሆን የሚያደርግ፤ በፍርድ ወይም ዉሳኔ የተገኘዉ መብት ወደ እዉነተኛ መብት እንዳይቀየር የሚያደርግ ነዉ፡፡ እንዲሁም በፍርድ የተረጋገጠን የግል ንብረት የሆነዉን የማይንቀሳቀስ ንብረት በፍርድ አፈጻጸም ለሌላ ወገን መስጠት ወይም መብት መፍጠር በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 40(1 እና 2) የዜጋን የግል ንብረት መብት መጣስን ወይም አለማስከበርን የሚያስከትል ስለሚሆን አግባብነት አይኖረዉም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በአፈጻጸም ክርክር ያስነሳዉ በዋናዉ ጉዳይ የተሰጠዉ ፍርድ ወይም ዉሳኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 153204 የካቲት 27 ቀን 2010 ዓ.ም ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ 155684 መስከረም 24 ቀን 2011 ዓ.ም ተሻሽሎ የተሰጠዉ እና በሰበር ሰሚ ችሎት የጸናዉ ዉሳኔ ነዉ፡፡ በተለይ በአፈጻጸም ክርክር ያስነሳዉና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ይዘቱ ቃል በቃል የሚለዉ ***"...ካርታ ቁጥሩ 83/6 የሆነዉ 3015 ካሬ ሜትር ይዞታና በላዩ ላይ የሰፈሩ ንብረቶች የተሸጠዉ ጌት እሸት ዲተረጀንት ማምረቻና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር አካል ነዉ ተብሎ የተሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ይህ ይዞታና ንብረት የአንደኛዉ ይ/ባይ(አሁኑ 1ኛ አመልች) ነዉ ተብሎ ተወስኗል፡፡"*** በማለት 3015 ካሬ ሜትር ይዞታና በላዩ የሰፈረዉ ንብረት የአሁኑ 1ኛ አመልካች መሆኑ በማያሻማ መልኩ ፍርድ አሳርፎበታል፡፡ ይህን ዉሳኔ ለማስፈጸም በካርታ ቁጥር 83/6 የሚታወቀዉን 3015 ካሬ ሜትር ከፍርድ በኃላ የፍርድ ባለመብቱ ተስማምቶበት ካልሆነ በቀር የፍርዱ መፈጸም በተጠሪዎች ላይ ከፍ ያለ ጉዳት የሚያስከትል ቢሆን እንኳ ከሌላ ይዞታ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቆርሶ ሳይካካስ ወይም ያለምን ማቻቻል ይዞታዉን ራሱን ለ1ኛ አመልካች በማስረከብ ፍርዱ እንዲፈጸም ሊደረግ የሚገባዉ ነዉ፡፡ ይህ መሆን ሲገባዉ የዚሁ ይዞታ አካል የሆነዉን ቆርሶ ለተጠሪዎች በመስጠት ከተጠሪዎች ይዞታ ላይ ደግሞ በመቀነስ አካክሶና አቻችሎ የነበረዉን የይዞታዉን ካርታ በማምከን አዲስ ካርታ በማሰጠት ማስፈጸም ከዋናዉ ፍርድ ዉጪ በመሆኑ ተገቢ ሊሆን አይችልም፡፡

በጥቂቱም ቢሆን ሊያሻማና ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችለዉ 3015 ካሬ ሜትር ይዞታን እንደነበረ ማስረከቡ ሳይሆን በላዩ ላይ የሰፈረዉ ንብረት የሚለዉ ጥቅል አገላለጽን የተጠቀመ በመሆኑ በተጠቃሹ ይዞታ ላይ የሰፈረዉን ፋብሪካ ጭምር ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ነዉ፡፡ ይህን ለመመለስ እየተፈጸመ ካለዉ የዉሳኔዉ ክፍል ባሻገር ሙሉ የፍርዱን ይዘት አመልካቾች ካቀረቡት ክስ ጀምሮ መመልከቱ ጠቃሚ ነዉ፡፡ በዋናዉ ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የካቲት 27 ቀን 2010 ዓ.ም ከሰጠዉ ፍርድ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካቾች ባቀረቡት ክስ ሁለት ዳኝነቶችን የጠየቁ ሲሆን የመጀመሪያዉ ጌት እሸት ዲተርጀንት ማምረቻና ማሸጊያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር አስመልክቶ ሕዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም የተደረገዉ የሽያጭ ዉል እንዲፈርስ፤ የማይፈርስበት በቂ ምክንያት ካለ ደግሞ የሽያጭ ገንዘቡን ተጠሪዎች እንዲከፍሉና በእጃቸዉ ያሉ ንብረቶች ኪራይ ታስቦ እንዲከፈላቸዉ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ የዳኝነት ጥያቄያቸዉ እና አሁን እያከራከረ ያለዉ ተጠሪዎች ከሕግ ዉጪ በያዙት 3015 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ተተክለዉ የሚገኙ የኬሚካል ኢንዱስትሪ ማሽኖች እና ሕንጻዎች ግምታቸዉ ብር 20,000,000 የሆኑ ንብረቶችን በነበሩበት ሁኔታ እንዲያስረክቧቸዉ፣ ያጡትን ገቢ እንዲከፍሏቸዉ፣ የንብረቶቹ ዋጋ ቅናሽ ተሰልቶና ያለአግባብ የበለጸጉበት ታስቦ እንዲከፈላቸዉ ዳኝነት የጠየቁበት ነዉ፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአመልካቾችን ሁለተኛዉን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ሲያደርግ የሰጠዉ ምክንያት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 38398 ሕዳር 04 ቀን 2009 ዓ.ም በኢ/ር ጌታቸዉ እሸቱ ስም በካርታ ቁጥር 83/6 በ3015 ካሬ ሜትር የሆነዉ ይዞታ በሽያጭ የተላለፈዉ ድርጅት አካል ነዉ በሚል ወደ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንዲዛወር በማለት ዉሳኔ ሰጥቶበት ዉሳኔዉ የተሻረ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት ይዞታዉንም ሆነ በይዞታዉ ላይ ያሉትን ንብረቶች የመመለስም ሆነ የእርጅና እና የተቋረጠ ጥቅም ተጠሪዎች ለአመልካቾች የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸዉ ሆኖ አልተገኘም በሚል የተወሰነ ነዉ፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት 2ኛ የዳኝነት ጥያቄ ላይም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የዳኝነት ጥያቄዉን ዉድቅ ሲያደርግ ከሰጠዉ ትንታኔ መገንዘብ የመሚቻለዉ በካርታ ቁጥር 83/6 በሆነዉ 3015 ካሬ ሜትር ላይ የሰፈረዉ አመልካቾች ንብረት በይዞታዉ ላይ የተተከሉ የኬሚካል ማሽኖች እና ሕንጻዎች እንዲሁም የሀረግ ትራንስፖርት መኪኖችን ያጠቃለለ እንጂ ምንነታቸዉ በትክክል ያልታወቁ ንብረቶችን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ ስለሆነም በ3015 ካ.ሜትር ይዞታ ላይ የሰፈሩ ሕንጻዎች፣ የኬሚካል ማሽነሪዎችም ሆኑ ማናቸዉም ንብረቶች የተጠሪዎች ነዉ የተባሉት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ ተከትሎ ይዞታዉም ሆነ ንብረቶቹ የተሸጠዉ ድርጅት አካል ናቸዉ ስለተባሉ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 155684 መስከረም 24 ቀን 2010 ዓ.ም በአፈጻጸም ክርክር ያስነሳዉን ዉሳኔ በሰጠበት የፍርድ ትንታኔ ክፍል ደግሞ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካቾችን 2ኛ የዳኝነት ጥያቄን አስመልክቶ የሰጠዉን ዉሳኔ ለመሻር 6 ተያያዥነትና ተደጋጋፊነት ያላቸዉን የተለያዩ ምክንያቶችን ዘርዝሮ ያስቀመጠ ሲሆን በ6ኛ ተራ ቁጥር ላይ "የኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በ3015 ካሬ ሜትር ይዞታ የፋብሪካዉ አካል ነዉ ብሎ በመ/ቁ 38398 የሰጠዉ ዉሳኔም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 189908 መሻሩ ተረጋግጧል" በማለት የስር ፍ/ቤቱ ለዉሳኔዉ ብቸኛ ምክንያት አድርጎ የሰጠዉን ምክንያት ዉድቅ ካደረገ በኃላ በይዞታ መለያ ቁጥር 83/6 የሆነዉ 3015 ካሬ ሜትር ይዞታና በላዩ ላይ የሰፈረዉ ንብረት የ1ኛ አመልካች መሆኑን በመግለጽ አሻሚ ባልሆነ መልኩ ወስኗል፡፡ ይህ ዉሳኔ ማስረጃዉን ያላገናዘበና ምክንያታዊ ላይሆን የሚችልበት ዕድል ሊኖር ይችላል፡፡ ፍርዱ ስህተት ያለበት፣ ማስረጃዉን ያላገናዘበ ወይም ምክንያታዊ ባይሆን እንኳ ፍርድ አስፈጻሚዉ ፍ/ቤት በምንም መልኩ በማስፈጸም ስበብ ፍርዱን ያለአግባብ ተርጉሞ ሊያቃናዉ አይችልም፡፡ ፍርዱ ሊፈጸም የሚገባዉ እንደፍርዱ በመሆኑ የይዞታ መለያ ቁጥር 83/6 የሆነዉ 3015 ካሬ ሜትርም ሆነ በላዩ ላይ የሰፈረዉ ማንኛዉም ንብረት ሕንጻዎች፣ የተተከሉ የኬሚካል ማሽኖች፣ ተሽከርካሪዎችን ጭምር ለ1ኛ አመልካች በማስረከብ ሊፈጸም የሚገባዉ ነዉ፡፡ ክፍፍሉ በተግባር መሬት ላይ አንድን ሕንጻ ለሁለት የሚከፍል ቢሆን እንኳ በዚሁ አግባብ ይፈጸማል እንጂ ሕንጻዉ ላይ የማምረቻ ማሽኑ ላይ ጉዳት ሳይደርስ ማካፈል አይቻልም ተብሎ ያለግራ ቀኙ ስምምነት ለአንዱ ጠቅልሎ ሰጥቶ ለሌላኛዉ ማካካሻ የሚሰጥበት የፍርድ አፈጻጸም ስርዓት የለንም፤ ሊፈቀድም አይገባም፡፡

በአጠቃላይ ፍርድ አስፈጻሚዉ የስር ፍ/ቤት በዋናዉ ፍርድ የካርታ ቁጥሩ 83/6 የሆነዉ 3015 ካሬ ሜትር ይዞታና በላዩ ላይ የሰፈሩት ንብረቶች በጠቅላዉ የተሸጠዉ የ3ኛ ተጠሪ ድርጅት አካል ሳይሆኑ የ1ኛ አመልካች ናቸዉ ተብሎ የተሰጠዉን ዉሳኔ ፍርድን በማስፈጸም ሰበብ ለ1ኛ አመልካች የተወሰነዉን ይዞታና በላዩ ላይ የሰፈሩትን ንብረቶች ማለትም ሕንጻዎች፣ የተተከሉ የኬሚካል ኢንዳስትሪ ማሽኖችና ንብረቶች ለተጠሪዎች እንዲሆኑና ከአመልካች ይዞታ የተወሰደዉን ይዞታ ከተጠሪዎች ባዶ ይዞታ ባማካካስ እንዲሁም አዲስ ካርታ እንዲሠራ በማድረግ እንዲፈጸም በማድረግ በአፈጻጸም አዲስ መብትና ግዴታን በሚፈጥር መልኩ የሰጠዉን የአፈጻጸም ዉሳኔ ከፍርድ አስፈጻሚዉ ፍርድ ቤት ስልጣን ዉጪና አመልካቾች በፍርድ የተጎናጸፉትን የንብረት መብት የሚሳጣ ሆኖ ስላገኘሁት አብላጫዉ ድምጽ የስር ፍ/ቤቶችን የአፈጻጸም ዉሳኔ ባጸናበት ዉሳኔ ባለመስማማት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ፋ/ዳ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !